# ወርሃዊ የአየር ጠባይ
# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከጃንዋሪ 1-31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከፌብሪዋሪ 1-28/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ፌብሪዋሪ 2022
አዲስ አበባ

| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|


ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ....... 3

ካርታ 6 ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....... 4

ካርታ 7 ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....... 5

ካርታ 8 ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....... 6

ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ....... 7

ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 7

ካርታ 9 ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 7

ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 8

ካርታ 10 ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 8

ኢ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 28/2022 የሚኖረው የአየር ....... 9

ጠባይ አዝማሚያ ....... 9

ኢ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 28/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 9

ኢ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 28/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 10


# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፈው የጃንዋሪ ወር የበጋዉ ደረቅ፣ ፀሃያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖባቸዉ ተስተዉሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የለሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት ላይ በሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ በደቡብና በምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ቦታዎች ላይ ጨምሮ ተስተዉሏል፡፡ ለአብነት ያህል በደብረዘይት 2.4፣ 4.2 እና 4.6 ፣ በአደሌ 3.0 እና 4.0፣ በሐረማያ -2.6፣ 1.0 እና 2.0፣ በአርሲ ሮቤ 3.0 እና 4.0፣ በቡኢ 3.0፣ 3.4 እና 4.0፣ በደብረብርሃን -2.4፣ -1.8፣ 0.0፣ 1.6፣ 1.8፣ 2.2፣ 2.4፣ እና 3.0፣ በዳንግላ 4.5፣ በሮቤ 4.0፣ 4.5፣ በደባርቅ 4.0፣ በእነዋሪ 4.5፣ በፍቼ 3.8፣ በመሀል ሜዳ 0.0፣ 1.8፣ 2.0፣ 4.0፣ 4.2 እንዲሁም በወገልጤና -1.0፣ 0.6፣ 1.6፣ 2.0፣ 2.5 እና 3.5 በዲግሪ ሴልሽየስ የገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል በጃንዋሪ በመጀመሪውና በተለይም በሁለተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በሰሜን ምሥራቅ፣ በመካከለኛው፣ በደቡብና በደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች አንፃራዊ ጥንካሬ በማሳየታቸው ምክንያት የደመና ሽፋን መጨመርና በአንዳንድ ቦታዎች ላይም ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ዘንቧል። ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከመዘገቡ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በቡኢ 68.0፣ በብላቴ 63.8፣ በሀዋሳ 55.0፣ በቦሬ 67.0፣ በዲላ 75.2፣ በሀገረማሪያም 33.6፣ በካቿሴ 31.2፣ በያቤሎ 46.0 እንዲሁም በወራቤ 41.3 በሚ.ሜ ይገኙባቸዋል፡፡


በወሩ ውስጥ የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ5-89 ሚ.ሜ. መጠን ያለው ዝናብ ከአማራ በዋግህምራ፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በደቡብ ጎንደር እና በምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፤ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ ቤንምቤላ፤ ከኦሮሚያ በኢሉባቦር፣ በጅማ፣ በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ በምዕራብ አርሲ፣ በሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ በጉጂና ቦረና ዞኖች፤ በአሶሳ እንዲሁም በአዲስ አበባ ላይ ከ5-89 ሚሜ የሚደርስ ከ1-13 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 6 እና 7) ፡፡

በወሩ ውስጥ የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር ከአማራ በዋግህምራ፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በደቡብ ጎንደር እና በምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሲዳማ፣ የጉራጌ፣ የሰገን ሕዝቦች፣ የደቡብ ኦሞ፣ የጋሙጎፋና የጌዶ፤ ቤንምቤላ፤ ከኦሮሚያ በኢሉባቦር፣ በጅማ፣ በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ በሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ በምዕራብ አርሲ፣ በጉጂና ቦረና ዞኖች፤ በአሶሳ እንዲሁም በአዲስ አበባ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀት የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 8) ፡፡


ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 7    ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 8 ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




## ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የጃንዋሪ ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ የሚያመዝንበት ወቅት ሲሆን፤ በአመዛኙ የድህረ ሰብል ሰብሰባ ተግባራት የሚጠናቀቁበትና ከወሩ አጋማሽ በኃላ በአንዳንድ የበልገ ሰብል አብቃይ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ተግባራትን ለመጀመር ዝግጅት የሚደረግበት ወቅት ነው።

ባሳለፍነው የጃንዋሪ ወር የበጋው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ (dry moisture condition) በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አመዝኖ እንደነበረ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን በተሟላ መልኩ ለማከናወን አዎንታዊ ሚና ነበረው። ሆኖም ግን በመጀመሪያው እና ሁለተኛው የወሩ አስር ቀናት በሰሜን ምሥራቅ፣ በመካከለኛው፣ በደቡብና በደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ላይ የእርጥበት መሻሻል እንደነበራቸውና በአንዳንድ ቦታዎች ላይም ከቀላል እስከ ከባድ መጠን የሚደረስ ዝናብ እንዳገኙ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም ሁኔታ የመጠጥ ውኃ አቅርቦትንና የአረንጓዴ እጽዋት ልምላሜ እንዲሁም የግጦሽ ሳር አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው። በተጨማሪም የተገኘው እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላትም ሆነ በቅርቡ የበልግ ወቅት የማሳ ዝግጅት አስቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች የአፈር ውስጥ እርጥበት እንዲሻሻል በጎ ተጽዕኖ ነበረው። በአንጻሩ ግን የነበረው የእርጥበት ሁኔታ የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ባላጠናቀቁ አካባቢዎች ላይ መጠነኛ አሉታዊ ጎን ነበረው (ካርታ 9)፡፡


ካርታ 9   ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ከጃንዋሪ 1-31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ ስንመለከተ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ እንደነበሩ ተስተውሏል፡፡ በዚህም መሰረት የላይኛውና የመካከለኛዉ ስምጥ ሸለቆ፣ የመካከለኛዉ ኦሞ ጊቤ፣ ዋቤ ሸበሌ እና በጥቂት የላይኛው ባሮ አኮቦ እንዲሁም የመካከለኛዉ አባይ እና አዋሽ ኪስ ቦታዎች ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ የነበራቸው ሲሆን፣ የተቀሩት ተፋሰሶች ከፊል ደረቅ እና ደረቃማ ሁኔታ ተፅዕኖ ስር ነበሩ (ካርታ 10) ፡፡

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 28/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

የፌብሪዋሪ ወር በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ የሚጀምርበት ጊዜ ነው፡፡ በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኋላ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ የደቡብ ምዕራብ፣ የደቡብ፣ የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የመካከለኛውና አጎራባች የስምጥ ሸለቆ ሥፍራዎች የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በመጪው ፌብሪዋሪ የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ ከወሩ አጋማሽ በኋላ ሊጠናከሩ እንደሚችሉና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ መጠነኛ መጠን ያለው ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ የምእራብ ኦሮሚያ ዞኖች በሆኑት ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ምሥራቅ ወለጋ፣ ጥቂት የአርሲ ዞን ሥፍራዎች፤ አዲስ አበባ፤ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በሚገኙት የቤንች ማጂ፣ ጉራጌና ሐዲያ፣ የወላይታ፣ የዳውሮ፤ ከአማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ዋግ ዞኖች አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። በአንፃሩ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።

# እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 28/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

የፌብሪዋሪ ወር በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ወቅት የመጀመሪያ ወር እንደመሆኑ በአብዛኛዎቹ የበልግ ሰብል አምራች በሆኑት አካባቢዎች የእርጥበት ይዘቱ በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኋላ ከቀን ወደ ቀን እየተጠናከረ የሚሄድበት ጊዜ ሲሆን፤ ከበልግ ስራ ጋር ተያይዞ በተለያዩ አካባቢዎቸ የማሳ ዝግጅት በስፋት የሚከናወንበት እና በአንዳንድ አካባቢዎችም አስቀድሞ ዘር መዝራት የሚጀምሩበት ወቅት ነው።

በተሰጠው የአየር ጠባይ ትንበያ መሰረት በመጪው ፌብሪዋሪ ወር የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ ከወሩ አጋማሽ በኋላ ሊጠናከሩ እንደሚችሉና ከዚሁም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ የተወሰነ መጠን ያለው እርጥበት ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የበልግ ወቅት አምራች በሆኑት አካባቢዎች የሚገኘውን አነስተኛ እርጥበት በመጠቀም የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና የተለያዩ የበልግ ወቅት ሰብሎችን አስቀድሞ በሚዘራባቸው አካባቢዎች ዘር ለመዝራት ለቋሚ ተክሎች የውሃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ይጠበቃል።

## እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 28/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው ፌብርዋሪ ወር የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተፅዕኖ ስንመላከት ቀስ በቀስ ከወሩ አጋማሽ በኋላ የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ሊጠናከሩ እንደሚችሉ እና በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ አነስተኛ የእርጥበት መጠን ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በአብዛኛዉ የአዋሽ፣ የአባይ፣ የላይኛውኛና የመካከለኛው ባሮአኮቦ፣ የስምጥሸለቆ፣ የኦሞጊቤ፣ በጥቂት የላይኛው ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የእርጥበት መጠን ሊያገኙ እንደሚችል የሚጠበቅ ሲሆን፤ በሌላ በኩል በዚህ ወር የቀኑ ሙቀት መጨመር ጋር ተያይዞ በውሃ አካላት ላይ ከፍተኛ የትንት መጠን የሚኖርበት ወቅት በመሆኑ የውሃ አጠቃቀማችን ለብክነት የሚያጋልጥ መሆኑን እንጠቁማለን፡፡